# የግንቦት 7 ድምጽ

የግንቦት 7 የፍትሕ፣ የነፃነትና የዴሞክራሲ ንቅናቄ፤ ሳምንታዊ ልሳን

www.ginbot7.org

አንብበው ያስነብቡ! አባዝተው ያሰራጩ!

ቁጥር 139 ጥር 5 2003 ገጽ 1


***አምባገነኖች የሚገዙትን ህዝብ ለመቆጣጠር ከሚወስዷቸው እርምጃዎች ቀዳሚው የመረጃ ፍሰትን መቆጣጠር ነው። እነሱ ከሚሉት ውጭ እንዳይሰማ ለማድረግ ወደ ህዝብ ጆሮ የሚደርሱትን ነገሮች ሁሉ የመቆጣጠር ተግባር ይፈጽማሉ። ከዚህም በተጨማሪ ውሸትን ደጋግሞ በማውራት እውነት ለማስመሰል ይተጋሉ። ይህ የአምባገነን ሥርዓቶች ሁሉ የጋራ ባህርይ ነው።***

ከግንቦት 7 ዕርሰ-አንቀጽ የተወሰደ (ገጽ-2)

## የትግራዩ ገዢ ጉጇሌ የሚያካሂደው ዘረኝነት በትምህርት መስክም ተጠናክሮ መቀጠሉ ታወቀ

ወያኔ ለድል አብቅቶኛል ብሎ የሚመጻደቅበትን የትግራይ ብሄረሰብ ዋና የድጋፍ መሠረቱ አድርጎ ለመቀጠል ባለው ስትራቴጂ ላለፉት 20 አመታት ክልሉን ኢሚዛናዊ የሆነ የኢኮኖሚ ተጠቃሚ ለማድረግ እያደረገ ካለው ጥረት በተጨማሪ በአገር ውስጥና ከአገር ውጪ የሚሰጡትን የትምህርት ዕድሎች ላይ በአመዛኙ የትግራይ ተወላጆች ከፍተኛውን የተጠቃሚነት ድርሻ እንዲይዙ እያደረገ መሆኑን ሰሞኑን ከትምህርት ሚንስተር አካባቢ የደረሱን መረጃዎች አጋልጠዋል።

እንደ መረጃ ምንጮቻችን ዘገባ ለፕሮፖጋንዳ ፍጆታ ተብሎ በተለያዩ ክልሎች ከተከፈቱት ከፍተኛ የትምህርት ተቋማት በውስጣዊ ድርጅታቸውና በሚሰጡት የትምህረት አይነትና ጥራት በእጂጉ እንደሚበልጡ ከሚነገርላቸው በትግራይ ውስጥ እንደ አሸን ከፈሉት የተለያዩ ኮሌጆች በተጨማሪ በአንጋፋነቱና ባሉት የመምህራን ደረጃ ከበረታ አለው በሚባለው የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲት የተለያዩ ዲፓርተመንቶች ውስጥ ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ያሉት የትግራይ ተማሪዎች ኮታ በማንኛውም የአገሪቱ ክልሎች ከሚኖሩት ብሄረሰቦች ሲነጻጸር ከፍተኛ ብልጫ እንዳለው ለማወቅ ተችሎአል። በዚህም የተነሳ በአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ የቴኪኒኦሎጂ ፋካሊት ውስጥ በዘንድሮው የትምህርት አመት ተመዝግበው ከሚገኙት ተማሪዎች ውስጥ 70 ከመቶ ፤ በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በምህንድስና (ኢን ጂነሪንግ) ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ከሚገኙት ተማሪዎች ደግሞ 90 በመቶ የሆኑት ተማሪዎች ትግሪኛ ቋንቋ ተናጋሪዎች እንደሆኑ ሲታወቅ ይህ ብዛት በአጋጣሚ የተከሰተ ሳይሆን ሆን ተብሎ በተደራጀና በተቀናበረ የዘረኝነት ፖሊሲ እየተመራ የተደረሰበት የመጠቃቀም ዘመቻው አካል ነው ተብሎአል።

በትምህርቱ ዘርፍ የወያኔው አገዛዝ እየፈጸመ ያለውን ግፍ አስመልክቶ ዘጋቢያችን ያናገራቸው አንድ ስማቸው እንዳይጠቀስ የፈለጉት የአዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ ባልደረባ እንዲህ አይነት አሠራር የወያኔ አገዛዝ የአገሪቱን የሥልጣን ማ ዕከል ከተቆጣጠረ ማግሥት ጀምሮ እየተገበረ ያለ እንደሆነና ተማሪዎቹን ብቻ ሳይሆን ቢሳካላቸውና የተማረ የሰው ሃይል ቢኖራቸው ኖር ትግሪኛ የማንናገረውን የግቢውን ሠራተኛ በሙሉ ጠራርገው በማባረር በራሳቸው ሰዎች ከመተካት የማይመለሱ ነበሩ ብለዋል።

አያይዘውም በትምህርቱ መስክ እየተወሰደ ያለው እንዲህ አይነት በፍጹም ዘረኝነት ላይ የተመሠረተ አሠራር የነገው አገር ተረካቢ የሆነውን ወጣት ትውልድ እድል ከማጨለም አልፎ ተጠቃሚ ለማድረግ የሚሞከረውንም (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኢትዮጵያ ህዝብ የዘረኛውን አገዛዝ ዘረፋ እየተቃወመ ነው

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የወያኔ አገዛዝ ለመጪዎቹ አምስት አመታት በእድገት ስም ላወጣው እቅድ እርዳታ መሰብሰብ በሚል ሰበብ ህዝብ ለመዝረፍ የጠነሰሰው አላማ የህዝብ ተቃውሞ ገጥሞታል።

ከአዲስ አበባ የደረሱን መረጃዎች እንደሚያመለክቱት፥ ገንዘብ እንዲያዋጡ በአገዛዙ ካድሬዎች ማስፈራራት እየተደረገባቸው ያሉት የመዲናይቱ ነዋሪዎች እምቢታቸውን በድፍረት እየገለጹ ነው። በወያኔው ሎሌ ኩማ ደመቅሳ የሚመራው የከተማይቱ መስተዳደር ስድስት መቶ ሚሊዮን ብር ከህዝብ ለመዝረፍ እቅድ አውጥቶ መነሳቱን ከዚህ ቀደም መዘገባችን ይታወሳል። ባለፉት በርካታ ሳምንታት ለዘጋቢያችን አመለካከታቸውን የገለጹ ነዋሪዎች እንኳን ለሚጠሉት አገዛዝ የገንዘብ ስጦታ ሊያደርጉ ይቅርና ምግብ መግዣም እንደሌላቸው በመናገር ሲያማርሩ ቆይተዋል።

አዲስ ነገር ኦንላይን የተባለው የዜና ድረ-ገጽም የመስተዳደሩን የዘረፋ ሙከራ መውደቅ አስመልክቶ ባቀረበው ዘገባ፣ ካድሬዎች ከቤት ቤት እየተዘዋወሩ በነዋሪዎች ላይ ተመን ሲጥሉ እና የተነገራቸውን መጠን ለመክፈል ፈቃደኞች ያልሆኑትን ሲያስፈራሩ እንደሰነበቱ ገልጿል። በዘገባው የተጠቀሰ አንድ ጸጉር አስተካካይም የተጠየቀውን ገንዘብ ካልከፈለ ስሙን በጥቁር መዝገብ ላይ እንደሚያስገቡ በመንገር ያስፈራሩትን ካድሬዎች ከቁብ ሳይቆጥር እምቢታውን አስታውቋል።

ዘረኛው እና አምባገነናዊው የመለስ ዜናዊ አገዛዝ በህዝብ ላይ እየፈጸመ ያለው ግፍ እና ዘረፋ ከመብዛቱ የተነሳ የኢትዮጵያውያን እሮሮ የሚፈነዳበት ደረጃ ላይ እንደደረሰ ይታወቃል። በርካታ አስተያየት ሰጪዎች ህዝቡ ወደ አመጽ ለመግባት የሚፈልገው ትንሽ ምክንያት ብቻ እንደሆነ ይናገራሉ። የግንቦት 7 ድምጽ ዘጋቢዎች በተለያዩ ከተሞች በመዘዋወር ያናገሯቸው ዜጎች በተጠሩ ጊዜ ለማመጽ ዝግጁ መሆናቸውን እንደገለጹ በቅርቡ መዘገባችን ይታወሳል።

ግዜ

ግንቦት 7 ዜና

## በወያኔ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የናረው የምግብ ሸያጭ ተመን አነጋጋሪ ሆኖ መሰንበቱ ተዘገበ

በወያኔ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የተፈጠረውን የኑሮ ውድነት ለማረጋጋት ተብሎ የወጣው የምግብ ሽያጭ ተመን አነጋጋሪ ሆኖ መሰንበቱ ተዘገበ።

የገና በአልን አስመልክቶ የጎጠኛው ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ የነግድ ማህበረሰቡን ሰብስቦ ያደረገው ንግግርና ያነን ተከትሎ የወጣው የዋጋ ተመን ሰሞኑን የህዝብ የመነጋገሪያ አጀንዳ ሆኖ መሰንበቱን ዘጋቢያችን ከአዲስ አበባ ከላከልን መረጃ ለማወቅ ተችሎአል።

የወያኔው አምባገነን አገዛዝ ሰሞኑን ያለወትሮው የህዝቡን ችግር በቁጥጥሩ ስር በሚገኘው የቴሌቪን ጣቢያ አማካኝነት ሲዘግብ የቆየ ሲሆን በድንገት ከንግዱ ማህበረሰብ ጋር ስብሰባ የተቀመጠው የአገዛዙ መሪ መለስ ዜናዊ ባልተጠበቀ ሁኔታ ነጋዴዎች የኑሮ ውድነት መንስዔ መሆናቸንና ይህንንም ለማሻሻል በሰላም ከመደራደር እጃቸውን እስከመቁረጥ የሚደርስ እርምጃ የሚወስድ መሁኑን በትእቢት መደንፋቱን ዘጋቢያችን ከስፍራው ከላከልን ሪፖርት ለማወቅ ተችሎአል ። ሪፖርተራችን ያነጋገራቸው አንዳንድ የአድስ አበባ ነዋሪዎች የመለስ ዜናዊ ስድብና ድንፋታ በንግድ ማህበረሰቡ ላይ ሽብርንና ተስፋ መቁረጥን የፈጠር እንደሆነና ይህም በተቀረው ህዝብ ዘንድ ከፍተኛ የመነጋገያ ርእስ ሆኖ መሰንበቱን ለማወቅ ተችሎአል።

በከተማዋ ለረዥም አመታት በንግድ ስራ ላይ የሚተዳደሩትና ስማቸው እንዳይጠቀስ የጠየቁ አንድ ባለሃብት በሁኔታው እጅግ ግራ መጋባታቸውን ገልጸው ‘ችግሩ ሁሉ የወያኔው አምባገነን አገዛዝ በሚቆጣጠራቸው ቱባ ቱባ በሚያከሉ የንግድ ድርጅቶች የተፈጠረ መሆኑን እየታወቀ እኛን ምን አድርጉ ይሉናል....እኛ ምን እንሁን’ በማለት ምሬታቸውን ገልጸዋል። ከውጭ አገር በመግባት ዘይት በማምረት ስራ ላይ የተሰማሩት አንድ ባለሃብት ደግሞ የዘይት እህሉን በጅምላ የሚያከፋፍሉት የወያኔ ድርጅቶች ራሳቸው እህሉን በከፍተኛ ዋጋ እየሸጡልን ተመርቶ የሚወጣውን ዘይት አገዛዙ በተመነበት ዝቅተኛ ዋጋ መሸጥ በድርጅታቸው ላይ ከፍተኛ ኪሳራ የሚያመጣባቸው መሆኑን ገልጸዋል። እኚሁ ባለሃብት አያይዘውም መለስ ዜናዊ ባለፈው ሳምንት ከነጋደው ህብረተሰብ ጋር ባደረገው ስብሰባ ወቅት እንደዛተው የአገሪቱ ዜጎች ተሰማርተውበት የሚገኙበትን ይህንን የንግድ ሥራ እንደሌላው የ እርሻና እንዱስትሪ መስክ ሰበብ ፈጥሮ ለቻይናና ለአረብ ባለሃብቶች አሳልፎ በመስጠት በሙስና ተጨማሪ ሃብት ለማከማቸት የታሰበ ወንጀል ከመሆን እንደማያልፍ ያላቸውን ጥርጣሬና ስጋት ገልጸዋል።

በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳዩ ያስገረማቸው አንድ አዛውንት ለዘጋቢያችን እንደገለጹት ወያኔ ሰሞኑን በቴለቪዥን ጣቢያው ሲያሳያቸው የቆየው ነገር (ወደ ገጽ 2 ዞሯል)

## የኖሮ ውድነት በከፍተኛ ፍጥነት እያሻቀበ መሆኑ ተገለጸ

ምንም እንኩዋን አይኑን በጨው ያጠበው አምባገነኑ የወያኔ ጎጠኛ ቡድን መሪ መለስ ዜናዊ በተደጋጋሚ ኢትዮጵያ በአለም ላይ በከፍተኛ ፍጥነት በማደግ ላይ ካሉ ሀገራት አንዱዋ መሆኑዋን በመጥቀስ ሲለፈልፍ የቆየ መሆኑ ቢታወቅም እውነታው ግን ከምንም ጊዜ በላይ አግጥጦ መውጣቱ ይህም ችግር በተለይም ባሰለፍነው የገና በአል ጎልቶ መታየቱን ዘጋቢያችን ከሥፍራው ከላከልን ዜና ለመረዳት ተችሎአል።

በግብር ከፋዩ የኢትዮጵያ ህዝብ ክፊያ የሚተዳደረውና ወያኔ የራሱን ፕሮፖጋና ብቻ ማራመጃ አድርጎ በሚጠቀምበት የአገሪቱ ቴሌቪዥን ጣቢያ ባልተለመደ መልኩ ሲተላለፍ በነበሩት የሰሞኑ ዝግጅቶች ላይ አስተያየታቸውን ለመስጠት እድል ያገኙ የአዲስ አበባ ነዋሪዎች የኑሮው ውድነቱ እንኩዋንስ መሀከለኛ ገቢ ያላቸው ቀርቶ ከፍተኛ ገቢ አላቸው የሚባሉትም እንኩዋን ሊቋቋሙት እንዳልቻሉና በዚህም የተነሳ አብዛኛዎቹ አስተያየት ሰጪዎች የዘንድሮው ገና በአል ባልተለመደ ሁኔታ እጅጉን ቀዝቀዞ እና ድምቀት ባልነበረው ሁኔታ ተከብሮ ማለፉን ገልጸዋል። በበዓሉ ዋዜማ አንዳንድ ጋዜጠኞች በአሉን እንደት ለመቀበል ተዘጋጅታችሁዋል በማለት ለህብረተሰቡ አቅርበውት በነበሩት ጥያቄዎች ከዚህ በላይ ምን ይመጣል በሚል ስሜት “ባዶ ቤትና ባዶ ሆድ ይዘህ ምን በአል አለ?” በማለት በሀዘን ሲናገሩ መስተዋላቸውን ዘጋቢያችን ገልጾአል። ከዚህም ጋር ተያይዞ አገዛዙ ከነጋዴው ህብረተሰብ ጋር ውይይት በማድረግ ስም እንደለመደው የከፋፍለህ ግዛ አላማውን ለማራመድ የንግድ ማህበረሰቡን ለችግሩ ሁሉ መንስኤ አድርጎ ሲኮንን መስተዋሉ ታውቆአል።

ዘጋቢያችን በበኩሉ ይህን በተመለከተ አስተያየት የጠየቃቸው አንዳንድ ነዋሪዎች እንደገለጹት ለዚህ ሁሉ ተጠያቂ የሆኑት የራሳቸው የወያኔ ድርጅቶች መሆናቸውን ሁሉም እንደሚያውቅ ተናግረው፤ እነመለስንም በዚህ ዘመን ማንንም በቀላሉ ሊያሞኙ እንደማይችሉ ያልተረዱ ሲሉ የገለጹዋቸው ሲሆን ይህም “አህያውን ፈርቶ ዳውላውን” የሚለውን አባባል እንዳስታወሳቸው ተናግረዋል።

ዘረኛው አምባገነን መለስና ግብረ አበሮቹ ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ በአዲስ አበባ ከተማ በግንባታ ላይ ያሉ ህንጻዎችንና በአለም አቀፍ ህብርተሰብ እርዳታና ብድር የተዘረጉትን መንገዶች ስፋትና ርዝመት በማስቆጠር ምን ያህል ስለማደጋችን እንደ መረጀ ሲጠቅሱ መቆየታቸው የሚታወስ ነው።

## ለነፃ ሚዲያ መኖር የምናደርገው ትግል የነፃነት ትግሉ አካል ነው!!!

አምባገነኖች የሚገዙትን ህዝብ ለመቆጣጠር ከሚወስዷቸው እርምጃዎች ቀዳሚው የመረጃ ፍሰትን መቆጣጠር ነው። እነሱ ከሚሉት ውጭ እንዳይሰማ ለማድረግ ወደ ህዝብ ጆሮ የሚደርሱትን ነገሮች ሁሉ የመቆጣጠር ተግባር ይፈጽማሉ። ከዚህም በተጨማሪ ውሸትን ደጋግሞ በማውራት እውነት ለማስመሰል ይተጋሉ። ይህ የአምባገነን ሥርዓቶች ሁሉ የጋራ ባህርይ ነው።

የትግራዩ ገዥ ጉጅሌ በጉልበት ሚኒሊክ ቤተመንግሥት ከገባበት እለት ጀምሮ እያደረገ ያለው ይህንኑ ነው። ጉጅሌው የመረጃ አውታሮችን ሙሉ በሙሉ ተቆጣጥሮ ቀንና ሌሊት ውሸቶችን እውነት ለማስመሰል ይጥራል። ኢትዮጵያ ውስጥ አማራጭ የመረጃ ምንጭ ስለሌለ አንዳንድ ወገኖቻችን ጉጅሌዉ ደጋግሞ የሚናገረዉ ዉሸት እዉነት ቢመስላቸዉ ልንፈርድባቸዉ አይገባም።
“የኢትዮጵያ” የሚል ስም ይዘው ኢትዮጵያን እየገደሉ ያሉ የሬድዮና የቴሌቪዥን ተቋማት እያደረጉት ያለው ምንድነው?

1. ኢትዮጵያዊያን በዘረኝነት እጅግ በተማረሩበት፤ አገሪቷ በአገር ውስጥ ቅኝ አገዛዝ ሥር ወድቃለች በሚባልበት በአሁኑ ወቅት ከላይ የተጠቀሱት ሚዲያዎች የሚያወሩት በወሬ ብቻ ስለፈጠሯት በአካል ግን ስለሌለችው ኢትዮጵያ ነው።
2. አጠገባቸው ሰቆቃ ሲፈፀም፤ ህፃናት ሲገደሉ፤ እናቶች ሲደፈሩ፤ ተማሪዎች ሲደበደቡ እያዩ “የኢትዮጵያ” ቴሌቪዥንና ራድዮ የሚያወሩት በወያኔ አገዛዝ ሰብዓዊ መብቶች የተከበሩ ስለመሆናቸው ነው።
3. ከአንድ ጎጥ የወጡ ሰዎች ቁልፍ ቦታዎችን ይዘው ሃገሪቷን እየቦጠቦጧት ባሉበት ባሁኑ ወቅት፤ በዘራቸው ከጎጡ አባላት ውጭ የሆኑት አጃቢዎች የምስለኔን ያክል እንኳን ሥልጣን የሌላቸዉ መሆኑ እየታወቀ፤ ዘርና ሃይማኖት መሠረት ያደረጉ ግጭቶች አገሪቷን እያመሷት እና እነዚህን ሁሉ በገዛ ዓይኖቻቸው እያዩ “የኢትዮጵያ” ቴሌቪዥንና ራድዮ የሚያወሩት ፍቅር ሞልቶ ስለመትረፉ እና የብሄር ብሄረሰቦች መብት ስለመከበሩ ነው።
4. እነዚህ ሚዲያዎች ወታደሩ፣ ፓሊሱ፣ ደህንነቱ እና ራሳቸው የሚዲያ ተቋማቱ ሁሉም በዘረኝነት የተተበተቡ፤ ከሙያዊ ኃላፊነት ይልቅ ለጆሮ ጠቢነት ይበልጥ ትኩረት የሚሰጡ መሆናቸው እየታወቀ ስለዚህ ጉዳይ ትንፍሽ የማይሉ፤ በግልባጩ “ውጤት-ተኮር”፣ ቢ.ፒ.አር. እያሉ የሚያደናግሩ አደንቋሪዎች ናቸው።
5. ፍርድ ቤቶች በፍትህ እያላገጡ ዋሾ ሚዲያዎች ትዕዛዝ የተሰጠባቸውን ዶሴዎች እየቆጠሩ ስለፍርድ ቤቶች “ምርታማነት” መጨመር ያወራሉ።
6. የገበሬው ማሳ ተቀምቶ ለባዕዳን በመሰጠቱ ምክንያት የበርካታ ቤተሰቦች ለቅሶ ሰሚ ባጣበት ወቅት እነኚህ የክህደት ሚዲያዎች ሚሊኒየነር ስለሆኑ ገበሬዎች ድራማ ሰርተው ያሳያሉ።
7. አገዛዙ ብር እያተመ፤ ድንገተኛ የውጭ ምንዛሪ ምጣኔ ለውጥ እያደረገ አውቆ የፈጠረውን የኑሮ ውድነት በችርቻሮ ነጋዴዎች ላይ እያሳበበ “ስግብግብ ነጋዴዎች” ያመጡት ውድነት ነው እያለ ህዝብን እርስ በርሱ ማባላት ሙያው አድርጎታል።
8. “ልማታዊ ጋዜጠኛ” እየተባለ የሚሸነገለው አድርባይ ጋዜጠኛ የኢትዮጵያ እናቶች ልጆቻቸውን በፈረቃ የሚመግቡበት ዘመን መሆኑን እያወቀ፤ ምናልባት በገዛ ራሱ ኑሮም ጭምር ተጨባጭ እውነታውን እያየው መዋሸት ስላለበት ይዋሻል። ጥቂት ዘረኛ የገዢው ጉጅሌ አባላትና ምስለኔዎቻቸው ህይወት የምድር ላይ ገነት መምሰሉ የኢትዮጵያ ህዝብ ኑሮ መሻሻል ምልክት ነው እያለ ዓይኑን በጨው አጥቦ ይነግረናል።
9. የመለስ ዜናዊ ተንኮለኛ “ብልጣ ብልጥነት” የአመራር ብቃት መመዘኛ አለመሆኑ መላው ዓለም እየተረዳ ባለበት፤ በአፍሪካ የመሪዎች የብቃት ምዘና መለስ 32 ከመቶ አምጥቶ መውደቁን ይፋ በሆነበት በአሁኑ ወቅት “ልማታዊው” ዋሾ ጋዜጠኛና ሚዲያው ስለመለስ የአፍሪካ ግንባር ቀደም መሪነት ይደሰኩራል።

ይህ ዓይነቱ ሚዲያ ነው አሁን የኢትዮጵያን አየር ያጣበበው።

ሰሞኑን ደግሞ በነፃ ሚዲያ ስም ስምንት የውሸት ማሰራጫዎች እንደሚከፈቱ ተነግሯል። የአንደኛው ባለቤት በእርግጠኝነት ይታወቃል የወያኔው ፋና ነው። ፋና ወያኔ ከበረሃ ጀምሮ ይዞት የመጣው ሬድዮ ነው። እስከዛሬ ፋና ሬድዮ በነፃ ሬድዮነት ስም “ከኢትዮጵያ” ሬድዮ በላይ ሲዋሽ ኖሯል። አሁን ደግሞ ፋና ቲቪ ከኢቲቪ በላይ ለመዋሸት አኮብኩቧል። ለጊዜው ስማቸውን ባናነሳም የቀሩት ሰባቱም መሠረታቸው አንድ እንደሆነ እናውቃለን።

ይህ ሁሉ በአንድነት ሲስተዋል የነፃ ሚዲያ አስፈላጊነትን እጅግ አንገብጋቢ ያደርገዋል። ለመሆኑ

- ዘወትር ስለፈጣን ግስጋሴ ቢነገረውም የሚበላውን ያጣውን የኢትዮጵያ ህዝብ፣ የትግራይ ገዢ ጉጅሌ አባላትና ምስለኔዎቻቸው ስለሚያጋብሱት ገንዘብ ማን ሹክ ይለዋል?
- በጋምቤላ ገበሬ ላይ የደረሰው በደል በከፋም፣ በአሶሳም፣ በሲዳማም እየደረሰ መሆኑን እና በደሉ መላው አገሪቷን ያጠቃለለ መሆኑን ለህዝባችን ማን ይነግረዋል?
- በኢኮኖሚ ለማደግ በአብዮታዊ ዲሞክራሲ መጠመቅ የማያስፈልግ መሆኑን የሌሎች አፍሪቃ አገሮች ልምድ እያጣቀሰ ማን መረጃ ይሰጠዋል?
- በአገራችን ያለው ዘረኝነት በቶሎ ካልተገታ ወደ አስከፊ አዘቅት የሚወስደን መሆኑ ከዚሁ መንገድ ተጉዘው መራር ጽዋ ከተጎነጩ አገሮች ልምድ ጋር አስታኮ ማን ይነግረዋል?

የኢትዮጵያ ህዝብ እውነት መች እና በምን ይሰማል?

እነዚህ ነገሮች ሁላችንንም ሊያስጨንቁን የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው። ስለሆነም ለእውነት የቆመ ነፃ ሚዲያ መወለድና ማበብ መታገል የትግላችን አንዱ አካል ተደርጎ መወሰድ ይኖርበታል።

ግንቦት 7 የፍትህ፣ የነፃነትና የዲሞክራሲ ንቅናቄ የነፃ ሚዲያ ጥቅምን ጠንቅቆ ይገነዘባል። ለእውነት የቆሙ ነፃ ሚዲያዎች መኖር ፍትህ የሰፈነባት ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ለመገንባት የምናደርገውን ትግል ያግዛሉ። ራሷ ዲሞክራሲያዊት ኢትዮጵያን ያለ ነፃ ሚዲያ ማሰብ አይቻልም። የንቅናቄዓችን አባላትና ደጋፊዎችም ለነፃ ሚዲያ መፈጠርና ማበብ የሚያደርጉት አስተዋጽኦ ለነፃነታችን የምናደርገው ትግል አካል መሆኑን ይገነዘባሉ። መረጃ የተጠማው የኢትዮጵያ ህዝብም ነፃ የሚዲያ ተቋማት እንዲፈጠሩና እንዲጠናከሩ የሚደረገውን ትግል እንዲደግፍ ጥሪ እናደርጋለን።

● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ● ●

### የትግራዩ ገዢ ጉጂሌ የሚያካሂደው ዘረኝነት በትምህርት . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

ቡድን ጥቅም አያስከብርም በማለት በሩዋንዳ በሁቱና ቱቲሲ መካከል የተፈጸመውን ዘግናኝ የብቀላ ጦርነት አስታውሰዋል። ላለፉት በርካታ አመታት ወደ ውጪ አገር ለከፍተኛ ትምህርት እየተላኩ ያሉ ወጣቶች ሆን ተብሎ በአብዛኛው የትግራይ ተወላጆች እንዲሆኑ እየተደረገ እንደሆነ፤ በአገር ቤት ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ የትግራይ ተወላጆች የዝሆን ድርሻ እንዲኖራቸው እየተመቻቸ መሆኑን፤ ትምህርታቸውንም ሲጨርሱ ሌሎችን በመግፋት በተለያዩ የሥራ ሃላፊነቶች ላይ እንዲሰማሩ እየተደረገ እንደሆነ በተለያዩ አጋጣሚዎች ሲገለጽ መቆየቱ አይዘነጋም።

በተያያዜ ዜና ዘረኛው የወያኔ አገዛዝ በኢትዮጵያ የሁለት አሃዝ እድገት አስመዘገቤያለሁ፣ የተለያዩ የግምባታ ስራዎችን ከመቼውም ጊዜ በላይ አከናወኛለሁ እያለ ለመኩራራት ቢጥርም እውነታው ግን ዘረኝነትን ማ ዕከል ባደረገ የራሱን ብሄረሰብ የአገሪቱን ከፍተኛ የፖለቲካ ሥልጣንና ሃብት እስከወዲያኛው ለመቆጣጠር እንዲችል የማደረግ ዘመቻ አካል መሆኑን ከተለያዩ ምንጮች እየደረሱን ያሉት ማስረጃዎች ያሳያሉ።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ ሰሞኑን በላከልን ዘገባ እንደገለጸው በሃገሪቱ ዋና ከተሞች በተለይም በአዲስ አበባ እየተገነቡ ያሉት ምርጥ ህንጻዎች በአገዛዙ ባለስልጣናትና ከአገዛዙ ጋር ቁርኝት ባላቸው የአገዛዙ ደጋፊዎች ባለቤትነት ይዞታ ሥር የሚገኙ መሆኑን የከተማውን አስተዳደር ምንጮች ዋቢ በማድረግ ገልጾአል፣ ፣ በዚህም መሰረት በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለፉት 10 አመታት የተገነቡትና በመገንባት ላይ ካሉ ዘመናዊ ህንጻዎች ከ90 በመቶው በላይ ከህወሃት ጋር ቅርበት ያላቸው ትግሪኛ ተናጋሪዎች ሃብት መሆኑን ለዚሁም መረጃ ከአዲስ አበባ ኡራኤል በቴክርስቲያን ጀምሮ እስከ መገናኛ ባለው አንድ መስመር ብቻ ከተገነቡትና በመገንባት ላይ ካሉት 68 ዘመናዊ ህንጻዎች 63ቱ የትግራይ ተወላጆች ንብረት መሆናቸው ታውቋል።

ዘረኛው አገዛዝ በተለይ ከግንባታ ጋር በተያያዘ የህዝብን ንብረት እየዘረፈ ወደ ጥቂቶች እጅ ሲያስተላልፍ እንደቆየ፣ በርካቶች ከአገዛዙ ባለስልጣናት ጋር ያላቸውን ቅርበት ወይም የዘር ትስስራቸውን በመጠቀም ህንጻዎችን በመገንባት ስም፣ የዋጋ ግሽበትን ከግምት ባላስገባ ወለድ ከመንግስት ባንኮች ከሚፈልጉት ገንዘብ በላይ ሲሰጣቸውና ብዙዎቹም ለህንጻው ግንባታ ከሚፈልጉት መጠን የተረፈውን ገንዘብ ወደ ውጭ ሃገራት ሲያሸሹ እንደቆዩ በስፋት ተዘግቡአል።

### በወያኔ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የናረው . . . (ከገጽ 1 የዞረ)

በሌላ በኩል ግን ችግሩ ወያኔዎቹ ራሳቸው የፈጠሩት እና የደረሰበትንም ያአስከፊነት ደረጃ ጠንቅቀው የሚያውቁት መሆኑን ጠቁዋሚ እንደሆነ ተናግረዋል። አዛውንቱ እንዳሉት የወያኔው አገዛዝ ቁንጮዎች ከዚህ በፊት ተሃድሶ ብለው የሚፈልጉትን ሰው ሊመቱ በፈለጉ ጊዜ እንዲህ አይነት ዘዴ የተጠቀሙ መሆኑን አስታውሰው ይህ የሰሞኑም ዘገባ ከጀርባ አንድ ተንኮል እንዳለው ያላቸውን ግምት ገልጸዋል።

ይህንኑ ጎዳይ እንዲያብራሩልን ዘጋቢያችን ያናገራቸው የምጣኔ ሀብት ሙሁር ወያኔ ከዚህ በፊት የውጭ ምንዛሪ ሲቸግራቸውና የሚሰርቁት ብር ሲደርቅባቸው በብዙ ሺህ ሄክታር የሚቆጠር ለም መሬት ያለምንም ጥናት ለውጭ ባለሃብቶች መቸብቸባቸው የሚታወቅ ሲሆን ይህም በውጭም ሆነ በአገርቤት ከፍተኛ ተቃውሞ እንዳስነሳባቸው ጠቁመው ከዛ ስህተት በመማር በሚመስል መልኩ ትንንሽ የሚሉዋቸውን ሀገር በቀል ነጋዴዎችን በህዝቡ ዘንድ የችግሩ ሁሉ ምክንያት አድርጎ በማቅረብ ከህዝቡ ጋር ካጣሉዋቸው በሁዋል ትልልቅ የውጭ ባለሃብቶችን በማስገባት እና ከራሳቸው ድርጅቶች ጋር በጋራ እንዲሰሩ ለማድረግ የታቀደ እንደሆነ ጠቁመዋል። ይህም ከፍተኛ ሃብት ለመዝረፍ ሊያመቻቸው የሚችል መሆኑን ጠቁመው ሀገሪቱን ግን እጅግ ወደከፋ የችግር አረንቋዋ የሚዘፍቃት እንደሚሆን አያይዘውም ተናግረዋል።

በተያያዘ ዜና ባለፈው ሳምንት የአምባገነኑ የወያኔ አገዛዝ ቁንጮ መለስ ዜናዊ ነጋዴዎች የሚሸጡአቸውን ሸቀጦች ዋጋ ዝርዝር ጽፈው በየሱቆቻቸው እንዲለጥፉ መመሪያ ካስተላለፈ ወዲህ ሰበብ አስባብ እየተፈለገ ነጋዴዎቹን የማስፈራራትና አንዳንድ ሱቆችንም የማሸግ ስራ መጀመሩን የግንቦት ሰባት ድምጽ ዘጋቢ ከአዲስ አበባ በላከልን ዘገባ ለማወቅ ተችሎአል።

(ወደ ገጽ 3 ዞሯል)



የፖስታሳጥን ቁጥር :- POBox: 4916
2003EX Haarlem, The Netherlands

## የህወሃት ዕድሜ አልፋና ኦሜጋ ለሚመስላቸው አባላቶቹና ደጋፊዎቹ አጭር መልዕክት

በየካቲት ወር 1968 ዓም ይፋ የሆነው የመጀመሪያው የህወሃት የፓርቲ ፕሮግራም መግቢያ ላይ:- "ትግራይ አክሱም እስከወደቀችበት ድረስ የአክሱም መንግሥት እየተባለች ትጠራ ነበር። አክሱም ከወደቀችም በኋላ እራሷን በማስተዳደር ለረጅም ጊዜ ብትኖርም ቅሉ አልፎ አልፎ ባካባቢዋ ለነበሩት ነገሥታት ግብር መክፈሏ አልቀረም። በአጼ ዮሃንስ ዘመነ መንግሥት ሃይሏ በርትቶ በአካባቢዋ የነበሩትን ነገሥታት በቁጥጥሯ ሥር አውላ ነበር። ይሁን እንጂ አጼ ዮሃንስ ከሞቱ በኋላ በዳግማዊ ምኒልክ አማካኝነት ትግራይ በሸዋው ማዕከላዊ ግዛት ሥር ወደቀች። ከዚህ በኋላ ነው የአማራው መሳፍንት ቡድንና ተከታዮቹ የትግራይን ነፃነት ገፈው የህዝቧን አንድነት ያናጉት። ግልጽና ስውር በሆኑ ዜደዎችም (ሸዋዊ ዘይቤዎች) የትግራይ ህዝብ በድንቁርና፤ በበሽታ፤ በረሃብ አዘቅት ውስጥ እንዲሰጥም ያደረጉት። በተለይም ትግሬነቱን በፍጥነት እንዲክድና ያለውዴታው በግዴታ አማራ ለማድረግ ያልሞከሩት ነገር ባይኖርም መሬቱ ተቆራርሶ ስለተወሰደበትና የተደራረበ ጭቆና ስለደረሰበት አገሩን ጥሎ ተሰደደ" ይላል።

ይህ የዛሬ 35 አመት ድርጅቱን በመሠረቱት በነ መለስ ዜናዊ የተጻፈው ባለ 39 ገጽ ሰነድ፤ ወያኔ ጫካ በነበረበት የትግል ዘመን የትግራይን ወጣቶች ለማነሳሳትና ከጎኑ ለማሰለፍ እንደመቀስቀሻ የተጠቀመበት የፕሮፖጋንዳ አጀንዳ ብቻ ሳይሆን ህወሃት ላለፉት 20 አመታት የአገሪቷን ከፍተኛ የሥልጣን እርከን ለመቆጣጠር ባገኘው እድል በአገሪቱ ውስጥ ለሚያወጣቸው ፖሊሲዎችና ለሚያከናውናቸው ተግባሮች እንደዋና መመሪያ አድርጎ እየተጠቀመበት ያለ ሰነድ መሆኑን በብዙ ማስረጃዎ አስደግፎ ማቅረብ ይቻላል። ለምሳሌ፤

1. የትግራይ ማዕከላዊ መንግሥትነት በአጼ ዮሃንስ ሽንፈት ወደ ሸዋ ተዛውሮብናል ተብሎ ለተቀሰቀሰው ቁጭት እና ብሶት በጻረ ደርግ ትግል በለስ የቀናው ህወሃት የአገሪቱን በትረ ሥልጣን ለመቆጣጠር ዕድል አንዳገኘ መከላከያውን፤ ደህንነቱን፤ የፖሊስ ተቋሙን፤ የፍርድ አካላቱን ጨምሮ ቁልፍ የሆኑ የአገሪቱን የፖለቲካ ሥልጣን መቀመጫዎች ሙሉ በሙሉ በትግራይ ልጆች ቁጥጥር ሥር እንዲውል በማድረግ ዮሃንስ የተነጠቁትን ሥልጣን ማስመለሱን አረጋገጠ፤
2. "ትግራይ መሬቷ ተቆራርሶ የተወሰደባትና ተወላጆቿም ለስደት የተዳረጉባት ነው" ለተባለው ብሶት ማካካሻ ከህወሃት ድል ማግሥት ጀምሮ ለም ከሚባሉት የጎንደር፣ የወሎ እና የአፋር ግዛቶች:- እነ ወልቃይት ጠገዴ፤ ጸለምት፤ ሁመራ ራያ፣ ኮረም፣ ከፊል ቆቦ ውቅሮ ወዘተ የመሳሰሉት ቦታዎች ወደ ትግራይ እንዲጠቃለሉ ከመደረጋቸውም በላይ፤ በሰፈራ ምክንያትና በተለያዩ ሥራዎች በመላው አገሪቱ ተሰማርተው ይኖሩ የነበሩትን የትግራይ ተወላጆች ወደ ተስፋይቱ ምድር እንደሚሰባሰቡ ቤተ-እስራኤሎች በዘመቻ (ከፊሎቹም ያለውዴታቸው) ወደ ክልላቸው እንዲመለሱ የማድረጉ ጥረት ህወሃት አዲስ አበባን በተቆጣጠረ ከአመት ባነሰ ጊዜ እንዲጠናቀቀ ተደረገ፤
3. "የትግራይ ህዝብ ግልጽና ስውር በሆነ ዘዴዎች (ሸዋዊ ዘይቤዎች) በድንቁርና፤ በበሽታ፤ በረሃብ አዘቅት ውስጥ እንዲሰጥም ተደርጓል" ተብሎ በህወሃት ፕሮግራም ውስጥ የሰፈነውን ብሶት ለመቅረፍ በአገራችን ታሪክ ታይቶ በማይታወቅ ፍጹም ዘረኝነት የአገሪቱ ሃብትና ንብረት በዘረፋ ወደ ክልሉ እንዲዞር ተደርጎ ዛሬ በትግራይ ልማት ማህበር ሥም በየጓዳውና በየጉራንጉሩ የተከፈቱት ዩኒቨርሲትዎች፤ ትምህርት ቤቶች፤ ሆስፒታሎች፤ ፋብሪካዎች፤ መንገዶች፤ ህንጻዎች፤ የመብራትና ውሃ አገልግሎቶች ፤ የእርከን ቋጠሮና የመስኖ ልማቶች፤ ለገበሬው የሚታደሉ የብድር አገልግሎቶች ወዘተ ድንቁርናውን፤ ረሃቡንና በሽታውን በቁጭት ከዚያች ምድር ነቅሎ የማጥፋት ዘመቻ አካል ነው፤
4. "ትግሬነትን በግዴታ ለማስለወጥ እና አማራ እንዲሆን የማድረግ ወንጀል ተፈጽሞአል" ለተባለው ክስ አማራ የሆነው ሁሉ ዋጋ እንዲከፍል የበቀል ዘመቻ ተከፍቶበታል። ከዚህም የተነሳ አማራ በገዛ አገሩ አንገቱን ቀና አድርጎ እንዳይሄድ ነፍጠኛ፤ ትምክህተኛ፤ የድሮ ሥርዓት ናፋቂ ወዘተ...በሚል ስድብ ስብዕናን ከማዋረድ ጀምሮ በሰበብ አስባቡ ከሥራ በማፈናቀል፤ በፖለቲካ ተቃውሞ ስም በመግደል፤ በየእስር ቤቱ በተወረወሩት ላይ ለመስማት የሚሰቀጥጥ ኢ-ሰብአዊ ሰቆቃ መፈጸም፤ ለምሳሌ በቅርቡ ይፋ እንደሆነው እንደ ወ/ሮ እማዋይሽ አይነቶቹን ሴት እስረኞች ጡቶቻቸውን በኤሌክትሪክ ገመድ በመግረፍ፤ የወንዶች ብልት ላይ የጠርሙስ ውሃ እየተንጠለጠለ የዘር ፍሬያቸው እንዲኮላሽ ማድረግ፤ እጅ እግራቸውን የፊጥኝ ታስረው እንዲንጠለጠሉ ማድረግ፤ ሆን ተብሎ ከኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊና ማህበራዊ ጥቅሞች እንዲገለሉ በማድረግ በቀል እርምጃ እየተወሰደ ነው።

ከሰሞኑ ለህዝብ ይፋ በተደረገው ዜና እንደተዘገበው ደግሞ ከአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የተማሪዎች ምዝገባ ክፍል በተገኘው መረጃ መሠረት በዩኒቨርሲቲው የቴክኖሎጂ ፋካሊቲ ውስጥ ትምህርታቸውን በመከታተል ላይ ከሚገኙ ተማሪዎች 70 ከመቶ የሆኑት ከትግራይ ክልል የመጡ ናቸው። በሲቪል ሰርቪስ ኮሌጅ በምህንድስና (ኢን ጂነሪንግ) ትምህርታቸውን እየተከታተሉ ከሚገኙት ተማሪዎች ደግሞ 90 በመቶ የሚሆኑት እንዲሁ ትግሪኛ ተናጋሪ ወገኖቻችን ናቸው። በአዲስ አበባ ከተማ ውስጥ ባለፉት 10 አመታት የተገነቡትና በመገንባት ላይ ካሉ ዘመናዊ ህንጻዎች ከ90 በመቶው በላይ ከህወሃት ጋር ቅርበት ያላቸው ትግሪኛ ተናጋሪዎች የሚያስተዳድሩት በአንድ ጀንበር ከህዝብ በተዘረፈ ሃብት የተገኙ ናቸው። የግንቦት 7 ድምጽ ከአዲስ አበባ ከተማ አስተዳደር የውስጥ ምንጮች ባገኘው መረጃ ከአዲስ አበባ ኡራኤል በቴክርስቲያን ጀምሮ እስከ መገናኛ ባለው አንድ መስመር ብቻ ከተገነቡትና ግንባታቸው ያልተጠናቀቁ 68 ዘመናዊ ህንጻዎች 63ቱ የትግራይ ተወላጆች ንብረት መሆኑ ታውቋል።

ህወሃት በተመሰረተ ገና በአመቱ በ1968 ይፋ ባደረገው የድርጅቱ የትግል መመሪያ ውስጥ የዘረዘራቸውን አላማዎቹን አንድ በአንድ ለመተግበር መልካም አጋጣሚ አግኝቶአል።

ይህንን አጋጣሚ ኢትዮጵያዊያን በአገራቸው የመጣ መከራና ስቃይ አድርገው ይመለከቱታል። በተለይ በትምህርቱ መስክ የነገው አገር ተረካቢ የሆነውን ወጣት ትውልድ እድል ለማጨለም ተብሎ በፍጹም ዘረኛነት ላይ በተመሠረተ ፖሊሲ የአንድን ቋንቋ ተናጋሪ በሁሉም የትምህርት መስክ ብቸኛ ተጠቃሚ ማድረግ የሚጎዳው አገሪቱን ብቻ ሳይሆን ዛሬ እየተጠቀመ ያለ የሚመስለውን ጭምር እንደሆነ መልሰው መላልሰው ቢናገሩም ወያኔን ፍጹም የሚያሳስበው አይመስለም። ላለፉት በርካታ አመታት ወደ ውጪ አገር ለከፍተኛ ትምህርት እየተላኩ ያሉ ወጣቶች ሆን ተብሎ በአብዛኛው የትግራይ ተወላጆች እንዲሆኑ ማድረግ፤ በአገር ቤት ባሉ ከፍተኛ የትምህርት ተቋሞች ውስጥ የዝሆን ድርሻ አንዲኖራቸው ማመቻቸት፤ ትምህርታቸውንም ሲጨርሱ ሌሎችን በመግፋት በተለያዩ የሥራ ሃላፊነቶች ላይ እንዲሰማሩ ማድረግ ውሎ ሲያድር ሊጎዳቸው ይችላል በማለት ወትውተዋል።

በጎረቤት አገር በሩዋንዳ ለተፈጠረው እልቂት እርሾ የነበረው ቅኝ ገዥዎች ልክ እንደወያኔ የአገዛዝ ዘመናቸውን ለማራዘም በሁቱና በቱትሲ መካከል በዘር ላይ የተመሰረተ ኢ-ሚዛናዊ የጥቅም ግንኙነት እንዲፈጠር ማድረጋቸው ነውና ይሄ ነገር ለአገራችን አይበጅም በማለት ተማጽነዋል፤ ከወደ ቤተመንግስቱ ግን የሰማቸው ግን ያለ አይመስልም። ጄኖሳይድ ዎች የተባለው አለማቀፍ ድርጅት ዳይሬክተር የሆኑት እና የቀድሞ የአሜሪካ የውጭ ጉዳይ ቢሮ ባለሥልጣን ዶ/ር ግሪጎሪ ስታንተን በቅርቡ በድህረ ምርጫ 97 በአጋዚ የተጨፈጨፉትን ሰማዕታት ለመዘከር በዋሽንግተን ዲሲ በተደረገው ስብሰባ ላይ እንደተናገሩት መለስ ዜናዊና ጥቂት ግብረአበሮቹ ዛሬ በአገራችን እየፈጸሙት ያለው በዘረኝነት ላይ የተመሰረተ መድልዎ ውሎ ሲያድር የሚጎዳው በመጀመሪያ ዛሬ እየተጠቀመ ያለውን መሆኑን መርሳት የለብንም ሲሉ ተደምጠዋል። ለዚህም የህወሃት እድሜ አልፋና ኦሜጋ የሚመስላቸው የትግራይ ወገኖቻችን ልብ ሊገዙና ለፍትህ፤ ነጻነትነ እና ለዲሞክራሲ የሚደረገውን ትግል መቀላቀል ያለባቸው ለራሳቸውና ለልጅ ልጆቻቸው ዋስትና እንጂ ለሌላ ብለው እንዳልሆነ ሊገነዘቡት ይገባል እንላለን።

## በወያኔ የተሳሳተ የኢኮኖሚ ፖሊሲ የናረው . . . (ከገጽ 2 የዞረ)

እንደ ዘጋቢያቹን ሪፖርት በአዲስ አበባ የተለያዩ ክፍለ ከተሞች የሚገኙ የንግድ ድርጅቶች የወያኔው አምባገነን አገዛዝ እያደረሰባቸው ባለው ማዋከብ እና አጋጣሚውንም በመጠቀም ካድረዎች በወሰዱት እርምጃ ለረጅም ጊዜ በንግድ ሥራ ላይ ተሰማርተው የነበሩትና ከአገዛዙ ምንም ጥበቃ የማያገኙ የንግዱ ህብረተሰብ ክፍሎች ከፍተኛ የሆነ ስቃይ ውስጥ ወድቀዋል። በተለይም የ ዕለት ጉርሳቸውን ለማግኘት ሲሉ በአንስተኛ የቺርቻሮ ሥራ ላይ ተሰማርተው የቆዩ አነስተኛ ነጋዴዎች ቀደም ሲል በውድ ዋጋ ከአከፋፋዮች ገዝተዋቸው የነበሩትን ሸቀጦች በኪሳራ ለመሸጥ መገደዳቸውንና በዚህም ምክንያት የመፈናቀል አደጋ እያንዣበበባቸው መሆኑን ተያይዞ የደረሰን ዜና ያስረዳል። ከዚሁም ጋር ተያይዞ በርካታ ሱቆች ለምን የሸቀጦችን ዋጋ ዝርዝር አልለጠፋቹሁም በሚል ሸፋን ሱቆቻቸው እየታሸጉባቸው መሆኑን ዘጋቢያቹን ተዘዋውራ ያነጋገረቻቸው ነጋዴዎች ገልጸውላታል።

በአሁኑ ሰአት በከፍተኛ ፍርሃትና ስጋት ውስጥ ከወደቁት ነጋዴዎች አንዳንዶቹን ተዙዋዝሮ ያነጋገረው ዘጋቢያችን፣ ህብረተሰቡ በዝቅተኛ ዋጋ ሸቀጦችን መግዛት የሚችልበትን ዕድል መፍጠር መልካም ቢሆንም ከአቅርቦት ጋር ያልተመጣጠነ የዋጋ ቅነሳ ለፖለቲካ ፍጆታ አጭርና ጊዜያዊ መፍትሄ ያስገኝ እንደሆን እንጂ ለዘለቀታው መፍትሄ አይሆንም ማለታቸውን ገልጾአል። አገዛዙ እውነተኛ የዋጋ መረጋጋትን ለመፍጠር ከልቡ የሚሠራ ቢሆን ኖሮ በህወሃት ሥር የሚተዳደሩ ግዙፎቹ የንግድ ድርጅቶች ቀረጥ ያልተከፈለባቸውን ዕቃዎች ከመነገድ እንዲታቀቡና ለሚሠሩት የንግድ ሥራ ግብር እንደማንኛውም እንዲከፍሉ ማድረግ በተቻለ ነበር ብለዋል ። ግዙፎቹ የወያኔ ኩባንያዎችና የንግድ ተቋማት እንዳሻቸው እንዲሠሩና በነጋዴው ህብረተሰብ ጫንቃ ላይ አንዲጨፍሩ እየተለቀቀ ከአገዛዙ ጋር የጥቅም ወይም የዘር ንክኪ የሌለንን ምን አድርጉ እንደሚሉን መገመት ከምንችለው በላይ እየሆነብን መጥቶአል በማለት ነጋዴዎች እያማረሩ ነው።

## በኢትዮጵያውያን ስደተኞች ላይ የሚደረገው ማሳደድ ተጡዋጡፎ መቀጠሉ ተገለጸ

ጎጠኛው የወያኔ ቡድን የፈጠራቸውን ሰው ሰራሽ ችግሮች ሽሽት በየጎረቤት ሀገራቱ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ከየሚኖሩባቸው ሀገራት መንግስታት ጋር በመደራደር በግዴታ ወደ አገርቤት እንዲመለሱ እያደረገ መሆኑ ይታወቃል፥ ፤ ሰሞኑን ደግሞ በደቡብ ሱዳን የሚታየውን የፖለቲካ ትኩሳት ምክንያት በማድረግ በሱዳን ሃገር በስደት ላይ የሚኖሩ ኢትዮጵያውያን እንዴት እየተለቀሙ ለወያኔው አገዛዝ ተላልፈው እየተሰጡ እንደሆነ ዘገባዎች ያሳያሉ፤ ፤ በዚህም መሰረት ብሉ ናይል የሚባለው የሱዳን ክልል አስተዳዳሪ ማሊክ አጋር እና የቤንሻንጉል ክልል ፕሬዝዳንት አህመድ ናሲር አልኩርሙክ በተባለችው የሱዳን ከተማ ስምምነት ላይ መድረሳቸውን ሱና የተባለው የሱዳን የዜና አገልግሎት ይፋ አድርጎአል። እንደዘገባው ከሆነ ይህ ዘመቻ በከተማዋና በዙሪያው በስደት በሚኖሩ በብዙ መቶዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን ላይ ያነጣጠረ መሆኑን አያይዞ ገልጹዋል።

የግንቦት ሰባት ዘጋቢ በጉዳዩ ላይ ያናገራቸውና በአካባቢው ይኖሩ የነበር እና በቅርቡ ወደ ለንደን መግባት የቻሉ አንድ ኢትዮጵያዊ እንደገለጹት በስፍራው በዘረኛው የወያኔ አገዛዝ ግፊት የሱዳን ባለስልጣናት በኢትዮጵያውያኑ ሰደተኞች ላይ እየደረሱት ያለው ግፍ እጅግ ፈታኝ መሆኑን ገልጸው በተለያዩ ጊዚያቶችም የወያኔ ወታደሮች ወደ ከተማዎቹ ዘልቀው በመግባትና የፈለጉትን ገለው የሚሄዱባቸው አጋጣሚዎች ብዙ መሆናቸውን ገልጸዋል። የሱዳን ባለስልጣናቱም ሆን ብለው የተባበሩት መንግስታት የስደተኞችን ሁኔታ እንዳያውቁ እንደሚያደርጉ፡ ይህም የወያኔው አገዛዝ ወታደሮች በስደተኞች ላይ የፈለጉትን እርምጃ መውሰድ እንዳስቻላቸው ጠቁመዋል።

በተመሳሳይ ሁኔታ በኬንያ የሚኖሩ ኢትዮጵያዊያን ስደተኞችን የተለያዩ የፖለቲካ ተቁዋሚዎች ናችሁ በሚል ስም የወያኔው አገዛዝ ወታደሮች በፈለጉበት ጊዜ ወደ ኬንያ በመግባትና የፈለጉትን ገለው የፈለጉትን አፍነው እንደሚወስዱ ባካባቢው ከሚገኙ ባለስልጣናትም ጋር በመተባበር ኢትዮጵያውያኑ በጅምላ እንዲባረሩ እንደሚደረግ ቀደም ብለን መዘገባችን ይታወሳል።

## በአገራቸው የሚካሄደውን የኬንያ ፖሊስ በአንድ ሳምንት ውስጥ ብቻ ሁለት ሺህ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን አስሬያለሁ አለ

የኬንያ ፖሊስ የፈረንጆቹ አዲስ አመት ከጀመረ አንስቶ እስከ አርብ ድረስ ብቻ ሁለት ሺህ ህገ-ወጥ ኢትዮጵያውያን ስደተኞችን ማሰሩ ተዘገበ።

ደይሊ ኔሽን የተባለው የኬንያ የዜና አውታር እንደዘገበው፥ ድህነትን ሽሽት ወደ ኬንያ የሚፈልሱ ኢትዮጵያውያን ወጣቶች ቁጥር በአገሪቱ ላይ ከፍተኛ ጫናን እያደረገ ነው። የታሰሩ፣ የተከሰሱ እና በጅምላ ወደ አገራቸው እንዲመለሱ የሚደረጉ ኢትዮጵያውያን ወሬ በሞያሌ አካባቢ የተለመደ እንደሆነም አውታሩ ጠቅሷል። ወጣቶቹ ወደ ኬንያ የሚገቡት ስራ ፍለጋ ወደ ደቡብ አፍሪካ ለማቋረጥ ነው ያለው ደይሊ ኔሽን፤ የራሳቸውን እና የቤተሰባቸውን ንብረት እየሸጡ ለአመላላሽ ደላላዎች እንደሚከፍሉም ዘግቧል።

በዘረኛውና አምባገነናዊው መለስ ዜናዊ የሚመራው የትግራይ ገዢ ጉጅሌ በኢትዮጵያ የኢኮኖሚ እድገት አስገኝቻለሁ እያለ በሚፎክርበት፤ በየአመቱ በአስርተ ሺሆች የሚቆጠሩ ዜጎች የተሻለ ኑሮ ፍለጋ እናት አገራቸውን እየጣሉ እንደሚሄዱ ይታወቃል። እንደ ፈረንጆች አቆጣጠር በ2009 ብቻ ከ42 ሺህ በላይ ኢትዮጵያውያን በተለያዩ አገራት የፖለቲካ ጥገኝነት መጠየቃቸውን የተባበሩት መንግስታት የስደተኞች ጉዳይ ኮሚሽን መግለጹ ይታወሳል። ይህ ቁጥር ግን ህገ-ወጥ የኢኮኖሚ ስደተኞችን እንደማያካትት ከዚህ ቀደም ጠቅሰናል።

ስደተኞቹ ስራ ፍለጋ ወደሚሄዱባቸው አገራት ለመድረስ ከፍተኛ አደጋን የሚጋፈጡ ሲሆን፤ ቁጥራቸው በውል የማይታወቅ ኢትዮጵያውያን መንገድ ላይ ይሞታሉ፤ በርካቶችም በእስር ላይ ይገኛሉ። ታዋቂው የዜና አውታር ሲ.ኤን.ኤን. ባለፈው ሰኞ እንደዘገበው፣ ስደተኞችን የጫኑ ሁለት ጀልባዎች በየመን ድንበር ላይ ከሰጠሙ በኋላ ከ80 በላይ የሚሆኑ ተሳፋሪዎቻቸው ሞተዋል ተብሎ እንደሚገመት እና ከነዚህም ብዙሃኑ ኢትዮጵያውያን እንደሆኑ ጠቅሷል።

## የአራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ተቃውሞን ተከትሎ የታሰሩ ተማሪዎች መድረሻቸው አልታወቀም

የአዲስ አበባው አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ ተማሪዎች በዚህ ሳምንት ተቃውሞ ማሰማታቸውን እና የዘረኛው አገዛዝ ፌዴራል ፖሊስ ወደ ግቢው መግባቱን የኢትዮጵያ ሳተላይት ቴሌቪዥን ድርጅት - ኢሳት - ዘግቦ ነበር።

ተቃውሞው የተነሳው የዩኒቨርሲቲው የኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነት ተከታይ ተማሪዎች የገናን በዓል በዩኒቨርሲቲው ግቢ ለማክበር ጠይቀው ከተከለከሉ በኋላ እንደሆነ ለማወቅ ተችሏል። የተማሪዎቹን ተቃውሞ ተከትሎም ባልታወቀ ምክንያት በተለያዩ ብሄር አባላት መካከል ግጭት ተነስቷል። የዩኒቨርሲቲው የሳይንስ ላይብረሪ መስኮቶች፣ እንዲሁም በግቢው ውስጥ ቆመው የነበሩ መኪኖች መሰባበራቸውን ኢሳት ዘግቧል።

ተቃውሞውን ለማስቆም ወደ ግቢው የገቡት የዘረኛው አገዛዝ ፌዴራል ፖሊስ እና የደህንነት ሰዎች አንዳንድ ተማሪዎችን እንዳሰሩ እና የእስረኞቹ እጣ ፈንታም እስካሁን እንደማይታወቅ ምንጮች ገልጸዋል። ፖሊስ በፈጸመው ድብደባ የተጎዱ ተማሪዎች እንዳሉም ለማወቅ ተችሏል።

ተማሪዎቹ በጸጥታ ሃይሎች የተወሰዱ ጓደኞቻቸው እንዲፈቱ ለመጠየቅ የረሃብ አድማ አድርገዋል። ይህ ዘገባ እስከተጠናቀረበት ጊዜ ድረስም አራት ኪሎ ዩኒቨርሲቲ እና አካባቢው ሲቪል እና ዩኒፎርም በለበሱ የዘረኛው አገዛዝ ቅጥረኞች ጥበቃ ስር እንደሚገኙ ምንጮቻችን ገልጸዋል።

ጉዳዩን በሚመለከት ለዝግጅፍ ክፍልችን አስተያየት የሰጡ የፖለቲካ ተንታኝ ተቃውሞው እንደተባለው እውነት ከገና በአል ጋር የተያያዘ ነው ብለው አያምኑም። የኢትዮጵያውያን ወጣቶች ተስፋ ከምንም ጊዜ በላይ የጨለመበት ጊዜ ላይ ነን ያሉን ግለሰብ፣ ተማሪዎቹ ቤተሰቦቻቸውን የተጋፈጠውን የኑሮ ውድነት እና ረሃብ፤ እንዲሁም እነሱን የሚጠብቃቸውን ስራ አጥነት እያሰቡ ቅሬታቸው እንደተካበ ገልጸዋል። እንደተቀረው ዜጋ ሁሉ የፖለቲካ ተቃውሟቸውን በግልጽ እንዳይገልጹ የታፈኑት ተማሪዎችም፣ የተለያዩ ሰበቦችን በማስታከክ ቅሬታቸውን እንደሚገልጹ አስረድተዋል። ወደፊትም ተመሳሳይ ተቃውሞዎች እንደሚከሰቱ ተንብየዋል።

# ማስታወቂያ

የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ፥ የትግራዩ ገዢ ጉጅሌ በስርጭቱ ላይ የሚፈጽምበትን አፈና ለመቋቋም የማያቋርጥ ጥረት እንደሚያደርግ ይታወቃል። ምንም እንኳ በአሁኑ ሰአት ስርጭቶቹ በተለያዩ የአገሪቱ ክፍሎች በጥራት የሚሰሙ ቢሆንም፤ ወደፊት ሊካሄዱ የሚችሉ ተጨማሪ የአፈና ጥረቶችን ለመቋቋም እና አድማጮች ጣቢያውን ለማግኘት ያላቸውን እድል ለማስፋት ሲል የስርጭት ሞገዶቹን ቁጥር ወደ ስምንት ከፍ አድርጎ፤ አንድ መካከለኛ ሞገድም የጨመረ ሲሆን፤ የስርጭት ሰአት ለውጥም ተደርጓል። አድማጮቻችን የሚከተሉትን ሞገዶች እና ሰአታት በመጻፍ ለምታውቋቸው ሁሉ እንድታስተላልፉ በአክብሮት እንጠይቃለን፡-

ቅዳሜ፥ ታህሳስ 23፣ 2003 ዓ.ም. ጀምሮ የግንቦት 7 ድምጽ ሬድዮ ስርጭት በሳምንት ሶስት ቀናት፤ ማለትም ማክሰኞ እና ሐሙስ፤ እንደ ኢትዮጵያ ሰአት አቆጣጠር ከጠዋቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30፤ በድጋሜም ከሰዓት በኋላ ከ11 ተኩል እስከ 12 ሰዓት፤ ቅዳሜ እንደ ኢትዮጵያ ሰዓት አቆጣጠር ከጠዋቱ 2 ሰዓት ተኩል እስከ 3 ሰዓት፤ በድጋሜም ከሰዓት በኋላ ከ11 ሰዓት ተኩል እስከ 12 ሰዓት፤

በ358 ሜትር ባንድ በ837 ኪሎ ኸርዝ መካከለኛ ሞገድ ላይ

በ31 ሜትር ባንድ በ9700 ኪሎ ኸርዝ ላይ

በ41 ሜትር ባንድ በ7185፣ በ7175፣ በ7160፣ እና በ7120 ኪሎ ኸርዝ ላይ

በ49 ሜትር ባንድ በ5980 ኪሎ ኸርዝ ላይ

በ60 ሜትር ባንድ በ4760 ኪሎ ኸርዝ አጫጭር ሞገዶች ላይ

የሚተላለፍ መሆኑን እናስታውቃለን። ከዚህም በተጨማሪ፥ ስርጭታችንን በሳተላይት ለመከታተል ለምትፈልጉ፤ በአረብ ሳተላይት፣ በ11980 ፍሬኩዌንሲ ላይ በተመሳሳይ ሰአታት ልታገኙት እንደምትችሉ እናሳስባለን።

የግንቦት7 ድምጽ ሬዲዮ

**የግንቦት 7 ድምጽ ሬዲዮ**
**የሥርጭት ሞገድ እንደሚከተለው ነው።**

**በ 7140፣ 7175፣ 7185 KHZ በ 41 ሜትር ባንድ እና በ 6100 KHZ በ 49 ሜትር ባንድ**

ላይ ዘወትር ማክሰኞ፣ ሐሙስ እና ቅዳሜ ከጠዋቱ 3፡00 ሰዓት እስከ 3፡30፤ እንዲሁም ከምሽቱ 2 ሰዓት እስከ 2፡30 የሚደመጥ መሆኑን እየገለጽን በወያኔ አፈና ምክንያት

**ውድ አንባቢዎቻችን**

ለፕሮግራማችን ይበጃል ያስተምራል ብላችሁ የምታሰቡትን መጣጥፋችሁን ለሬድዎን ክፍላችን ዎይም ለሳምንታዊው ጋዜጣ ክፍል በሚከተለው የኢ-ሜል አድራሻ ትልኩልን ዘንድ የአክብሮት ግብዛችንን እናቀርባለን። g7radio@ginbot7.org